

# የትንቢት ቃል

አምስተኛ ዓመት, ቁጥር2

ታሕሳስ 2003

ወቅታዊ የአድቬንቲስት መጽሔት

## የሱስ በቅርብ ይመለሳል - እንዴት ነው መኖር የሚገባን?

በህይወት የምትኖርበት ጊዜ ለጥቂት ሰዓታት ብቻ እንደሆን ብታውቅ ኑሮ ምን ታደርግ ነበር? ማለትም፥ ከዚህ አለም በሞት ልትለይ የቀሩህ ሰዓታት ጥቂት እንደሆኑ ብታውቅ ኑሮ ምን ታደርግ ነበር? በዚህ ጊዜ ላንተ በጣም አስፈላጊ የሆነው ነገር ምን ይሆን? በነዚያ ወሳኝ ሰዓታት ስለምን ወይም ስለማን ነበር የምታስበው? በአእምሮህ ውስጥ የሚመላለሰው ሃሳብ ምን ይሆን? በባንክ ቤት ስላከማቸከው ሃብት ወይስ ስትመኝ እንደነበረው አይነት ያማረና ሰፊ ቤት ሳትሠራ መቅረትህን ነው? ወይም ደግሞ ስትመኘው የነበረውን ትምህርት ተምረህ ሳትመረቅ መቅረትህን ነው የምታስበው? ወይስ ለረጅም ጊዜ ስትመኘው የነበረውን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሳትገዛ መቅረትህን ነው? በቴሌቪዥን ስትመለከት የነበረውን ተከታታይ ፊልም መጨረሻውን ሳታይ በመቅረትህ ታዝን ይሆን? ወይስ ሰዎች አንተን የበደሉህና መጥፎ ቃላቶች የተናገሩህ ጊዜያቶች ናቸው ትዝ የሚሉህ?

ልክ እንደእኔ ሞት አፋፍ ላይ የነበረ እና የዳነ ማንኛውም ሰው በዚያ የሞት ሰዓት ላይ ሲኖር ከላይ የጠቀስኳቸው ነገሮች ሁሉ ዋጋ እንደማይኖራቸው ይመሰክራል። ገንዘብ፣ሃብት፣ትምህርት፣አለማዊ ተድላዎች ሁሉ በሞት አፋፍ ላይ ለሚገኝ ሰው ትርጉም አይኖራቸውም። በተለይ በዚህ አይነት ሁኔታ ላይ ለሚገኝ ለአንድ ክርስቲያን ሁለት ወሳኝ ነገሮች አሉት፥- አንደኛ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው የግል ግንኙነት፤ሁለተኛ ደግሞ ከቅርብ ዘመዶቹ ጋር ያለው ግንኙነት ናቸው። በተለይ ከዘመድ አዝማድ ጋር ያለው ግንኙነት በጣም ወሳኝ ይሆናል። የሚለያቸው ዘመዶቹ በጌታ የማያምኑ ከሆነና ጌታ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ እንደማያገኛቸው ስለሚያውቅ በዚያች የሞት ሰዓት ላይ በጣም የሚያሳስበው ጉዳይ ይህ ይሆናል።

ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው ነገሮች ሁሉ ከዋናው ርእስ ጋር ምን ግንኙነት አላቸው? በርግጥ ለመናገር፥ ለሞት በመዘጋጀትና ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት በመዘጋጀት መካከል ምንም ልዩነት የለም። ሁለቱም ለክርስቲያኖች ተመሳሳይ ነገሮች ናቸው። ኤለን ዋይት ከዚህ ርእሳችን ጋር የሚሄድ አንድ ጥያቄ አቅርባ ነበር፥- «እንበልና ክርስቶስ ዛሬ በደመና ተመልሶ መጣ፤ ማን ነው እሱን ለመቀበል ዝግጁ ይሆን የነበረው?» በመቀጠልም እራሳችንን እንድንመረምር የሚያደፋፍረን ጥያቄ ጠየቀች፤ይህም ለመጀመሪያው ጥያቄ መልስ ሊሆን ይችላል፥- «ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለህ? ከእግዚአብሔር ጋር ተባብረህ እየሠራህ ነው? በአካባቢህ ላሉት ጌታን ለማያውቁት እያገለገልክ ነው? በቤተሰብህ ውስጥ ላሉት፣ለጎረቤቶችህ፣ለምታውቃቸው ሰዎች ሁሉ?» (ጀነራል ኮንፈረንስ ቡለቲን 6.ኤፕሪል 1903)



እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነትና ለሌሎች ወንጌልን የመናገር እነርሱንም የማዘጋጀት ኃላፊነት ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት እንዴት መዘጋጀት እንዳለብን የሚረዱን ሁለት አስፈላጊ ነጥቦች ናቸው። በዚህም በመመርኮዝ ቀጥለን የየሱስን ተመልሶ መምጣት በመጠባበቅ ላይ መሆናችንን ወይም አለመሆናችንን የሚመረምሩ አምስት ሃሳቦችን እንመለከታለን።

1) ዳግም ተወልደናል

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደዚህ ብሎ ይነግረናል፥- «ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በስተቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም (ዮሐ 3፥3)። የዳግም መወለድ ሥራ ከአእምሮ በላይ የሆነ የአንድ ሰው አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ የሚቀየርበት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ዳግም የተወለድን ለመሆኑ ጌታ የሱስ የሕይወታችን አላማ እና መካከለኛ መሆኑ ነው። «ለየሱስ ዳግም ምጽአት ተዘጋጅተሃል ወይ?» ለሚለው ጥያቄ የመጀመሪያው መልሱ ሐዋሪያው ዮሐንስ ገልጾታል፥- «እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንክ አንተን፣የላከውንም የሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት» (ዮሐ 17፥3)። በመሆኑም ዋናው ጥያቄ «በርግጥ እግዚአብሔርን አውቀዋለሁን?»

(በገጽ 3 ይቀጥላል)

## «የሚቤዠኝ ሕያው እንደ ሆነ አውቃለሁ»

ሴትየዋ ስለአሰቃቂ የግድያ ወንጀሏ የእድሜ ልክ እስራት የፍርድ ውሳኔ በሰማችበት ወቅትና ቀሪው የሕይወት ዘመኗ በነዚያ ጠባብ የእስር ቤቶች ውስጥ የሚያልፍ መሆኑንና ማምለጥም እንደማትችል ስትገነዘብ ተደነግጣለች። በጣምም ተስፋ ቆርጣ ከፍርድ ቤት ወደ ወህኒው ቤት እየሄደች ሳለች ከወህኒው ቤት ፊት ለፊት አንድ አዛውንት የመቃብር ጉድጓድ በአፈር ሲሞሉ ታስተውላለች። ወዲያውኑም ስለኚህ አዛውንት ማንነትና ምንስ እንደሚሠሩ ስትጠይቅ- እኚህ አዛውንት ሥራቸው የሞቱትን እስረኞች በሬሳ ሳጥን ውስጥ አድርጎ ከወህኒው ፊት ለፊት ባለው የመቃብር ቦታ መቅበር መሆኑን ተረዳለች። በዚህን ጊዜ እኚህ አዛውንት ለርሷ ከዚያ ወህኒ ቤት ነጻ መውጣት ወሳኝ እንደሆኑ ተገንዝባ ስለ አዛውንቱ ስትጠይቅ እውር እንደሆኑና ለመታከሚያ ገንዘብ የሌላቸው መሆኑን ተረዳለች። በዚህን ጊዜ ወደርሳቸው ቀረብ ትልና፥- «አባቴ፥ እኔን ከወህኒ እንድወጣ ከረዱኝ እኔም ለዓይንዎ መታከሚያ የሚሆን የአፕራሲዮን ገንዘብ እሰጥዎታለሁ» ትላቸዋለች። «እሜቴ- ይህንን ላደርግ

(በገጽ 7 ይቀጥላል)

### በዚህ እትም ውስጥ


| | |
|---|---|
| የሱስ በቅርብ ይመለሳል - እንዴት ነው መኖር የሚገባን? | 1 |
| የሚቤዠኝ ሕያው እንደ ሆነ አውቃለሁ | 1 |
| ከአዘጋጆች | 2 |
| ስም | 2 |
| ከአንባቢዎች | 2 |
| «በጌታ ደስ ይባላችሁ» | 3 |
| የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ መንስኤ ምንድን ነው? | 4 |
| ራእይ ሲገለጽ | 5 |
| የተስፋፋው ተቃርኖ - ክፍል 4 | 6 |
| እግዚአብሔር አዋቂ ነው | 7 |


Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# ከአዘጋጆች



***የተወደዱ አንባቢ ሆይ!***

በስምዎ ጠርተን ሰላም ብንልዎ ይበልጥ ደስ ይለን ነበር።

የትንቢት ቃል መጽሔትን ካነበቡ በኋላ ከየአቅጣጫው የሚያበረታቱ ደብዳቤዎችን የሚልኩልን ሰዎች ብዙዎች ናቸው። ሁሉንም ደብዳቤዎች በዚህች ትንሽ መጽሔት ማስተናገድ ባንችልም፣የሁሉንም መሠረታዊ ሃሳብ ያስተጋባሉ ብለን ያሰብናቸውን ሰላምታዎችና አስተያየቶች በየወቅቱ እናወጣለን።

ደብዳቤ ባይጽፉም ለመጽሔቷ በረከት የሚጸልዩም ብዙ ወንድምና እህቶች እንዳሉ ይሰማናል። የአንድ መንፈሳዊ መጽሔት መዋጣት የሚወሰነው ከእግዚአብሔር መንፈስ እርዳታ ቀጥሎ በአንባቢዎች ድጋፍ ነው። በጸሎት ፣ በአስተያየት፣ በመልእክቶች፣በገንዘብ ድጋፍ እና ሌሎች ነገሮች አንባቢያን ለወንጌል ስርጭት የግል አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ። የትንቢት ቃል መጽሔትም አንባቢያን በነዚህ በጠቀስናቸው ነጥቦች ድጋፍ ነው እስከዛሬ በሕይወት ያለችው ለማለት እንደፍራለን። ይህችም መጽሔት ሰዎች በቀላሉ ሊደርሱ በማይችሉበት ቦታ ታላቅ ሚና እየተጫወተች ስላለች ደስ ብሎናል። በወህኒ ቤት፣በበረሃ፣በጦር ሜዳ፣በአረብ አገሮች፣በተሸበሩ አገሮች፣...።

በዚህ አጋጣሚ ይህች በእጅዎ የያዟት ቁጥር ከእትማት ጀምሮ እስከ ስርጭት የሚያስፈልገውን ወጪ በድጋሚ ለሸፈኑልን በዋሺንግተን ዲሲ አመታዊ ስብሰባ ላይ የተገኙትን አድቬንቲስት ወገኖች ከልብ ልናመሰግን እንወዳለን። ስለዚህ የተቀደሰ አገልግሎታችሁ ስናስብ በ2ኛ ቆሮ 9፥6-7 ያለው ቃል ትዝ አለን፥- «በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፣በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል። እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወደዋልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፣በሃዘን ወይም በግድ አይደለም። »

ውድ አንባቢ ሆይ፥- እርስዎም በተሰጠዎ የጸጋ ስጦታ እንዲሁም የጌታ መንፈስ ባሳሰበዎ መጠን ለዚህች ወቅታዊ አድቬንቲስት መጽሔት በረከት ለሚያደርጉት አስተዋጽኦ እስቀድመን እግዚአብሔር ይባርክዎ እንላለን።

*የናንተው፥*

*ዳዊት መሐሪ እና ዳዊት መንግሥቱ*

## ወንጌል — ስም

ስም በተለይም የሰው ስም በዚያ ሰው ሕይወት ትልቅ ቦታ ያለው ቃል እንደሆነ ይታወቃል። ከአወጣጡ ብንነሳ ቤተሰብ ለአንድ አዲስ ልጅ በዘፈቀደ ስም አያወጣም። ተመክሮበት ታስቦበት በአብዛኛውም ብዙ አማራጮች ቀርበው አንዱ ይጸናል። ይህም ስም ለዚያ ሰው ካለው ትልቅ ዋጋ የተነሳ አንዳንዶች ስምን «በባለቤቱ ጆሮ ከሁሉ ጣፋጭ ቃል» ይሉታል። ይህንንም በራስዎ ለማረጋገጥ ሰው ሲጠራዎ «አንቺ/አንተ» ሲልዎት ነው ወይንስ «እገሌ፣ከበደ፣በቀለች፣...» ብሎ በስምዎ ሲጠራዎት ነው ደስ የሚልዎ?

ለማንኛውም በዚህ አይነት ስለ ስም ብዙ ማለት የሚቻል ሲሆን በዚህ ጽሑፍ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ ስሞች አንዱን ወስደን በዚያ ውስጥ ያሉ በረከቶችን ከውድ አንባቢዎቻችን ጋር ለመካፈል እንወዳለን።

**እግዚአብሔር ሰዎችን ሲገናኝ መጀመሪያ «ስማቸውን» ይቀይራል**

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ያሉ ስሞችም ሆነ የዛሬ ዘመን ስሞች በቋንቋቸው የራሳቸው ትርጉም አላቸው። ለምሳሌ የርስዎ ስም ማነው? ትርጉሙስ ምንድን ነው? እናምናለን ይህንን ጥያቄ በትክክል መልሰዋል። ወደ መጽሐፍ ቅዱስም ስንሄድ ሁሉም ስሞች ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ አንዳንድ ትርጉሞችንም ከዚያው እናጎላለን። ለምሳሌ «አማኑኤል» ማለት «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» ማለት ሲሆን «ሩሃማ» ደግሞ «ምህረት የሚገባት» ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ሌላው ተደጋግሞ የሚታየው እግዚአብሔር ሰዎችን ሲገናኝ ስማቸውን መቀየሩ ሲሆን ዛሬም በዚሁ አምድ በዋናነት የምናየው በዚሁ መልክ ስሙ የተቀየረውን የሐዋሪያ ጳውሎስን ስም ይሆናል።

ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ ጌታውን ከመገናኘቱ በፊት ስሙ ማን ነበር? «ሳውል»። በሌላ ቦታ ተመሳሳይ ስም የነበረው ሰው የሚያውቁት አለ? አዎን, ሳውል በእስራኤል ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ ንጉሥ በቁመናው ከሁሉ የተሻለ ጦረኛ ነበር። ጳውሎስም ከቢኒያም ማለትም ከነገሥታት ነገድ እንደመወለዱ ወላጆቹ እንደ ንጉሡ ይሆንላቸው ዘንድ «ሳውል» እንዳሉት እናያለን። «ሳውል» የሚለው የእብራይስጥኛ ስም «ከፍ ያለ ወይም የተከበረ» የሚል ትርጉም አለው። የአዲስ ኪዳኑ ሳውልም በሕይወቱ ሳውልነቱን የተቀበለ ይመስላል። በልጅነቱ ከታዋቂው የዘመኑ መምህር ገማልኤል እግር ስር በማደግ የአይሁድን ትምህርት ጠንቅቆ ያወቀ ሲሆን ይህንንም ትምህርት በሥራ ላይ ለማዋል «በዚህ በተማርኩት ትክክለኛ የእግዚአብሔር እውነት ላይ የተነሱ» ያላቸውን ክርስቲያኖች እስከማሳደድ ሲደርስ እናያለን። ነገር ግን ይህንን የተሳሳተ ተልእኮ ለመፈጸም በጉዞ ላይ ሳለ የሰማይ አምላክ ተገናኝቶ ጎዳናውንና ሁለንተናውን ሲቀይር፤ከተቀየሩት ብዙ ነገሮች አንዱ ስሙ ነበር። ሳውል የነበረው «ጳውሎስ» ተባለ ትርጉሙም «ታናሽ» የሚል ነው።

በመጀመሪያው ንጉሥ ስም የተጠራው ሳውል እጅግ የሚፈልገውን ታላቅነት ወደዚያም ግብ የሚያደርሱ ብዙ ነገሮቹን (ፊሊ.2፥8) እንደጉድፍ ቆጠራቸው። የእርሱን ትክክለኛ ማንነት እና ኃጢያተኝነቱን ተረዳ። የጌታውንና የአዳኙን የክርስቶስን ፍቅር ተረዳ። ስለዚህም የሚበልጠውና የሚሻለው ምድራዊ ከንቱ የሆነ «ታላቅነት» ሳይሆን ዘላለማዊውና በጌታው ሕይወት በሙላት የተገለጸው ዝቅ የማለት የፍቅር ታናሽነት ነበር። በእርግጥም ይሄ በሥጋዊ አይን ሲታይ እንደሚመስለው ዝቅተኛነት፣ውዳቂነት አልነበረም። በአንጻሩ ግን መንፈሳዊ አይኑን ያሳወረው ቅርፊት ሲወድቅ ለጳውሎስ የተገለጠለት ታላቅ መዝገብ ነበር። ስለዚህም ጳውሎስ ባለፈው እየተጸጸተ በደስታ ታናሽነትን (ጳውሎስነትን) ተቀበለ።

ውድ በጌታ የምንወድዎ፥- ዛሬ ጌታ ቢገናኝዎና ስምዎን ሊቀይር ቢፈልግ ይፈቅዳሉ? አዲሱ ስምዎ «ጳውሎስ» ቢሆንስ? በርግጥ ጌታን ያገኙና ወደ እርሱ አካልም በሙላት የተቀላቀሉ ከሆነ ዳግም እንኳን ደስ ያለዎት እያለን ስለዚህ ታላቅ በረከት አብረን ጌታን እናመሰግናለን። ካልሆነ ግን ይህንን ታላቅ ዘላለማዊ ሕይወት እና በረከት ዛሬ ይቀበሉ ዘንድ በጌታ ፍቅር እንጋብዝዎታለን። «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤አሮጌው ነገር አልፎአል እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል» (2ቆሮ5፥17)። ጌታ ይባርክዎ!◆

**አትክልት ኢሳያስ, አ.አ. ዩኒቨርሲቲ**

# ከአንባቢዎች

የጌታ ሰላምና ጸጋ ይብዛላችሁ እያልኩ ሰላምታዬን አቀርባለሁ። ውድ የትንቢት ቃል አዘጋጆች! ይህችን አጭር ደብዳቤ ስጽፍላችሁ ታላቅ ደስታ በውስጤ እየተሰማኝ ነው። ዋናው ነገር የእናንተ መጽሔት ተከታታይ ለመሆን ስለምፈልግ የትንቢት ቃልን እንድትልኩልኝ ነው። እግዚአብሔር አድማሳችንን ያስፋልን ብዙ ምርኮን ይስጠን በማለት እጸልያለሁ። እኔ አድቬንቲስት ነኝ ያለሁትም በወሎ ክ/ሃ ነው። እኔ በምገኝበት አካባቢ ጥቂቶቻችን ማለትም እኔና ቤተሰቦቼ ብቻ ነን። እግዚአብሔር እንዲያበዛን በጸሎታችሁ አስቡን። ጌታ ይባርካችሁ።

**እህታችሁ ዘውዲቱ ባዬ, ከኮምቦልቻ**

ዛሬ ተሳክቶልኝ ስለጻፍኩላችሁ እግዚአብሔር ይመስገን። ውድ የትንቢት ቃል አዘጋጆች የጌታ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። ከመቸውም ጊዜ በላይ የአድቬንቲስት ቤ/ክ እውነትና ጥሪውን ማስተላለፍ ሰዓቱና ጊዜያቱ አሁን ስለሆነ ይህንንም ለማሳካት የምታደርጉት የትንቢት ቃል አድቬንቲስት መጽሔት ስርጭት በአለም ዙሪያ ደስ የሚያሰኝ ነው። በምታደርጉት የተቀደሰ ሥራ ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ።

**እህታችሁ መሠረት ሶሬቻ, ከኢንግላንድ**

በክርስቶስ የሱስ ደም የተዋጃችሁ ውድ ወንድሞቼ የትንቢት ቃል አዘጋጆች፥- ምንም እንኳን በአካል ተገናኝተን ባንተዋወቅም አንድ አባት እግዚአብሔር ስላለን በልጁ ደም ተዋጅተን የአንድ ቤተሰብ አባል ሆነናልና በዚህ ደስ ይለኛል። በትንቢት ቃል በኩል ስለምታነቃቁን የሞተ ሕሊናችን በመንፈስ እንድነቃቃ ስለምታደርጉ «እኔስ ወዴት ነኝ? ለጌታ ሥራ ምን ያህል እየተጋሁ ነኝ?» እንድንል እናንተ በልዑል መጠጊያ ስር አርፋችሁ እኛም እንድናርፍና በመንፈሳዊ ሕይወት ወደፊት እንድንሮጥ ስለምትጋብዙን ጌታ ይባርካችሁ። የምታደርጉት መንፈሳዊ ሥራ በጣም የሚባርክና የሚያበረታታ ነው! ለኔ በዚህ ዘመን በደብዳቤ በመጻፍ የምታበረታቱን «ሐዋሪያው ጳውሎሶች» ብላችሁ ማጋነን አይሆንብኝም። እንግዲህ በጌታ በርቱ፤ይህ የመጀመሪያዬ ነው ወደፊትም እጽፋለሁ።

**ወንድማችሁ ስጦታው አማረ, ከወላይታ ሶዶ**

በመጀመሪያ ሰላምታዬ ይድረሳችሁ፤ የእግዚአብሔር

*(በገጽ 4 ይቀጥላል)*



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# «በጌታ ደስ ይባላችሁ»

## ወንጌል ከአገር ውጪ

ከጁላይ 3 2003 እስከ እለተ ሰንበት ድረስ በዋሺንገተን ዲሲ ተደርጎ የነበረው ጠቅላላ መንፈሳዊ ስብሰባችን በሚያስደስት አኳኋን የተከናወነ መሆኑን ስገልጽ የተሰማኝ ደስታ ለመናገር ቃላት ያጥሩኛል። ትምህርቱም ያተኮረው ከፊሊጵስዩስ መልእክት ውስጥ «በጌታ ደስ ይባላችሁ» በሚል ርእስ ላይ በመመርኮዝ ሰፊ ጥናትና ትምህርት የተደረገበት፣በጥያቄና መልስ ምእመናኑ በሰፊው የተሳተፉበትና እንዲሁም መንፈስን የሚያድሱ የጥንት ትዝታ የሚቀሰቅሱ መዝሙር የተዘመሩበት መንፈሳዊ ስብሰባ ነበር።

ያገሩም ርቀትም ሆነ የወጪውም ብዛት ሳይወስናቸው በቅድሚያ የተሰጣቸውን የትምህርት ክፍል አጥንተው፦ ፓስተር ግርማ ዳምጤ፣ፋሲል ከተማ፣ሥራዬ ደሴ፣መስፍን በላቸው፣እጅጉ ቶሎሳና ብርሃኑ ፀሐዬ በየተራ በመፈራረቅ መንፈስን የሚያድስ በበረከት የተሞላ የእግዚአብሔርን ቃል በተቀላጠፈ ሁኔታ አበርክተዋል።

ከእኛው ጋር እለተ ሰንበትን ለማክበር ከአንድ መቶ በላይ የሚሆኑ ምእመናን በመገኘት የበረከቱ ተካፋይ ሆነዋል። ከቀትር በኋላም ተደርጎ በነበረው የመደምደሚያ ስብሰባ ላይ ከምእመናኑ የተሰነዘረው አስተያየት ባጭሩ እንዲህ የሚል ነበር፦ «በርቱልን፣ይኸንን የመሰለ ስብሰባ ቀጥሉ፣የኢትዮጵያውያን አድቬንቲስት አንድነት ማህበር በመላ አሜሪካ ይቋቋምልን» በማለት ስሜታቸውን ገልጸዋል።

ያለፈው ዓመት በሲያትል ዋሺንግተን ተደርጎ በነበረው ስብሰባና ዘንድሮም ካሊፎርኒያ የተደረገው ስብሰባ አይነት ወደፊት ከቀጠለ ምእመናኑን ለሁለት በመክፈል ለከፍተኛ ወጪ መዳረጉ ግልጽ ነው። ድርጅቶቹ ባሉበት ክፍለ ሃገራቸው ተወስነው በየጊዜው በመሰብሰብ ማህበራቸውን ሊያዳብሩና ሊያጠነክሩ ይችላሉ።

በዋሺንገተን ዲሲ የሚገኘው ማህበር ከተመሠረተ ጊዜ አንስቶ በተሰጠው መምሪያና ደንብ መሰረት በሞላ አሜሪካና በካናዳ የሚኖሩትን ምእመናን ሁሉ በመወከል በየአመቱ የሚያደርግገውን አጠቃላይ ስብሰባ ሲያበረክት እነሆ አስር አመታት አልፎታል። ሁሌ የስብሰባው መጨረሻ ላይ የማህበሩን ሊቀመንበር የሚመርጠው ከየክፍለሃገሩ ከመጡት ምእመናን መካከል ነው። ለዚህም ለምሳሌ ያህል ፋሲል ከተማ ከሚዙሪ፣ አበበ ከካንሳስ፣ መላኩ ምህረቴ ከዲ.ሲ.፣ ሰለሞን ነጋሽ ደግሞ ከካሊፎርኒያ ተመርጠው አገልግሎት አበርክተዋል። ለወደፊቱም ቢሆን አንድ አላማ፣አንድ ገጽና አንድ አቋም ያለው ጠንካራ ድርጅት ቢቋቋም ማህበሩንም የሚመራ ኮሚቴ ከምእመናኑ መካከል ቢመረጥ ለመጪው ትውልድም ሆነ አሁን ላለነውም ቢሆን ጠቃሚ ነው። እያንዳንዱ ምእመን የድርጅቱ አባል ስለሆነ የአመቱን መዋጮ ይከፍላል።



ይህንን በመሰለ ሁኔታ ከተደራጀን ራሳችንን በመቻል ብቻ ሳንወሰን አገር ቤት የሚገኙትን የአድቬንቲስት ወገኖቻችንን በገንዘብም ሆነ በሌላ አገልግሎት ለመርዳት ያስችለናል።

«ለወገኔ ይጠቅማል በማለት እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትህትና ይቁጠር፤እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ» (ፊሊ. 2፥3-4)። ይህንን የጳውሎስ ምክር በተግባር ማዋል እንድንችል እግዚአብሔር ይርዳን።

**መላኩ ምሕረቴ, ከዋሺንግተን ዲሲ**

እ.ኤ.አ. የጁላይ 2003 ወር ግሩም የበረከት ጊዜ ነበር። በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ከጁላይ 3-5 በተደረገው መንፈሳዊ ጉባኤና ከጁላይ 24-27 በሳንሆዜ ካሊፎርኒያ ከተማ በተደረገው መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ በመገኘት የበረከቱ ተካፋይ ነበርኩ።

የዘንድሮውን ዓመት መንፈሳዊ ጉባኤ ልዩ የሚያደርጉ ነጥቦች መሃከል መጥቀስ ቢያስፈልግ ለእነዚህ ስብሰባዎች ዘወትር ማካሰኞ ቀን በሰሜን አሜሪካ እንዲሁም በአውሮፓ የሚገኙ አድቬንቲስት ምእመናን የተለየ ፀሎት ያደርጉ ነበር። እግዚአብሔር አምላክ ፀሎት ሰሚ ነውና በመንፈስ የተጠሙ ወገኖች ቃሉን ለመካፈል ከተለያዩ ከተሞች በጉባኤው ቦታዎች በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች ሁነዋል።

በዋሺንግተን ዲ.ሲ. ከተማ ስለተደረገው ጉባኤ ወንድም መላኩ ምህረቴ በዝርዝሩ ገልጾታል። በሳነሆዜ ካሊፎርኒያ ከተማ በተደረገው ጉባኤ ደግሞ እንግዳ ተናጋሪ የነበሩት አገልጋይ በኢትዮጵያ በሚሲዮናዊነት ሲያገለግሉ ቆይተው ወደ አሜሪካ የተመለሱት ፓስተር ጃክ ሰኩዌራ ነበሩ። ፕሮግራሙን ለመካፈል ከተለያዩ ከተሞች የመጡት አድቬንቲስት ምእመናን በበረከት ተሞልተው መንፈሳዊ ሕይወታቸው ታድሶ እንደተመለሱ ከሰጡት ምስክርነት ሰምቼአለሁ።



በስብሰባው ላይ ተካፋይ የነበሩ እናትና አባቶች የተለየ የፀሎት ጊዜ በመውሰድ ለልጆቻቸው መንፈሳዊ ሕይወትና በወጣትነት ዘመናቸው ለሚያጋጥሙአቸው ልዩ ልዩ ፈተናዎች በእግዚአብሔር ሃይል ማሸነፍ እንዲችሉና በሕይወታቸው እግዚአብሔርን በማስቀደም እንዲራመዱ እንዲችሉ ፀሎት አድርገዋል።

እነዚህ ጉባኤዎች የተሳኩ እንዲሆኑ ለረዳን ለሃያሉ አምላካችን ምስጋና እያቀረብን፤በሚመጣው አመት በዋሺንግተን ዲ.ሲ. እና በሲያትል ከተሞች መንፈሳዊ ጉባኤ ለማድረግ እቅድ ስላለ፤የእግዚአብሔር መሪነትና ጥበቃ ከሁላችን ጋር ሆኖ ለበረከቱ እንዲያበቃን ምኞቴና ፀሎቴ ነው።
«እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ተቀደሱ» (እያሱ 3፥5)◆

**ብርሐኑ ፀሐዬ, ሳንሆዜ ካሊፎርኒያ**

<u>*የሱስ በቅርብ ... (ከገጽ1 የዞረ)*</u>

የሚለው ነው። ስለሃይማኖት በመነጋገርና ከግል አዳኛችን ከጌታችን፣ከመሪያችንና ከወዳጃችን ከየሱስ ጋር ስለተለማመድነው ሕይወት በመነጋገር መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። ዳግም ያልተወለደ ሰው ከየሱስ ጋር እንደዚህ አይነት ግንኙነት ሊኖረው አይችልም። የሰማዩ አባታችን ምኞት ከእኛ ጋር የጠበቀና የቀረበ ግንኙነት እንዲኖረው ነው። እንደዚህ አይነት የጠበቀ ግንኙነት በምድር ሕይወታችን መለማመድ እንችላለን።

2) የእግዚአብሔርን ቃል የበለጠ ለማስተዋል ሙሉ ፍላጎት ይኖረናል።

ዳግም ከመወለዳችን በፊት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያሰለችና ለማንበብም የማይጥም መጽሐፍ ስለሚመስለን አናነበውም ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ከተወለድን በኋላ ግን ይህንን የእግዚአብሔር ቃል ለማንበብና ለማስተዋል የውስጥ ፍላጎት አለን። አስተሳሰባችንንም በቃሉ ውስጥ በተገለጠው እውነት ለመሙላት ፍላጎት አለን። ሐዋሪያው ጴጥሮስ፦ «ልክ አዲስ እንደተወለደ ህጻን እውነተኛውን ወተት እሹ» ይለናል (1ጴጥ2፥2)። መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ ፍላጎት መዳናቸውን ያረጋገጡና ለየሱስ ዳግም ምጽአት የሚዘጋጁ ሰዎች ልዩ ምልክት ነው። በተለይ በዚህ በምድር ታሪክ መጨረሻ ጊዜ የሚከሰቱትን ነገሮች ለመወጣት የምንችለው ቃሉን በስፋትና በጥንቃቄ ስናውቀው ብቻ ነው። «ነፍሱን በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ያጠነከረ ብቻ ነው የመጨረሻውን ታላቅ ተጋድሎ ሊቋቋም የሚችለው» (ታላቁ ተጋድሎ, 594)

3) በየእለቱ የማያቋርጥ የፀሎት ሕይወት ይኖረናል።
የዘላለም ሕይወት የሚያስገኘን

*(በገጽ 4 ይቀጥላል)*


Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com



# ጤናችን — የኤች.አይ.ቪ መንስኤ ምንድን ነው?

ኤች. አይ. ቪ በአይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ ረቂቅ ሲሆን አካልን የተፈጥሮ በሽታን የመከላከል ኃይሉን በማሳጣት ለተደራራቢ ሕመም የሚያጋልጥ እስከ አሁን ድረስ ምንም አይነት ክትባት ወይንም መድኃኒት ያልተገኘለት ቫይረስ ነው። ቢሆንም ግን በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ቦታዎች የሚደረጉት የሕክምና ሳይንስ ጥናቶች የተስፋን ጭላንጭል ያመለክታሉ።

**የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች ምንድን ናቸው?**

ኤች. አይ. ቪ በከፍተኛ መጠን በወንድ የዘር ፍሬ ፈሳሽ፣በሴት የብልትና የማሕጸን ፈሳሽ፣በደምና በደም ተዋፅኦ ውስጥ ይገኛል። በዝቅተኛ መጠን ደግሞ በጡት ወተት፣በምራቅ፣በእንባ፣በሽንትና ኀብለ ሰረሰር ፈሳሽ እንዲሁም በሌሎች ከሰውነት ከሚመነጩና ከሚወገዱ ፈሳሾች ውስጥ ሊገኝ ይችላል። ይሁንና እስከ አሁን ድረስ ከተገኘው ሳይንሳዊ መረጃ/ማረጋገጫ አንጻር ቫይረሱ አደገኛ የሚሆነው ከፍተኛ የቫይረስ ክምችት ከሚገኝባቸው የአካል ፈሳሾች ጋር በሚደረግ ግኑኝነት በመሆኑ በሚከተሉት ዋና ዋና መንገዶች ይተላለፋል።

ሀ) ከኤድስ በሽተኛ ወይም ኤች. አይ. ቪ ተሸካሚ ጋር በሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ማለትም በተለመደ የግብረ ሥጋና ባልተለመደ የግብረ ሰዶም ግንኙነት በመፈጸም

ለ) ከተበከለ ደምና የደም ተዋፅኦ ጋር በሚደረግ ንክኪ

- በኤች. አይ. ቪ የተበከለ ደም ከቫይረሱ ነጻ ስለመሆኑ ሳይታወቅ ለታመመ ሰው ሲሰጥ
- የቆሰለ የአካል ክፍል ወይንም ማንኛውም የአካል ክፍተት ከተበከለ ደምና የደም ተዋፅኦ ጋር በቀጥታ ሲነካካ
- በተበከለ መርፌ መወጋት። ይህ የመተላለፊያ መንገድ በተለይ የሚያጠቃው አደንዛዥ እጽ ለሚወስዱ ሰዎች ነው። በተጨማሪም በተበከሉ የስለት መሳሪያዎች መጠቀም ለቫይረሱ ያጋልጣል።
- እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ዘመናዊ የሕክምና አገልግሎት በደንብ ማግኘት በማይችሉ ሕዝቦች ዘንድ ጎጅ ባሕላዊ የሕክምና ዘዴዎች በመጠቀም ለምሳሌ ጉሮሮን በማስቧጠጥ፣ እንጥል በማስቆረጥና በማስገረዝ በመሳሰሉት ድርጊቶች ለበሽታው መተላለፍ አመቺ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

ሐ) ከእናት ወደ ልጅ በመተላለፍ

የኤድስ በሽተኛ ወይንም ኤች. አይ. ቪ በደምዋ ውስጥ ያለ እናት በእርግዝና ጊዜ በሽታው፣ በወሊድና በአራስ ቤት በጡት ወተት አማካይነት ከእናት ወደ ልጅ ይተላለፋል።◆ *ይቀጥላል*

*ከአንባቢዎች (ከገጽ 2 የዞረ)*

ጸጋ ይብዛላችሁ እላለሁ። የትንቢት ቃል ከእናንተ ሲደርሰኝ እጅግ በጣም ደስ ስላለኝ በዚህ አጋጣሚ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ። እናንተም ሆነ እኛ በያዝነው የልብ እምነት ከጸናንና ወንድምና እህቶቻችንን ካጽናናን ይህ መልካም ስለሆነ በርቱ፣ጠንክሩ። ለሚሰማና ለሚያዳምጥ ሁሉ ጥሩ መልእክት አለው። ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትሉ ወንጌልን አስተላልፉ። በአሁኑ ወቅት የእግዚአብሔር ቃል እንደ እንጀራ የሚርባቸውና እንደ ውሃ የሚጠማቸው ሰዎች ስላሉ ትምህርታችሁን በማስፋፋት መበርታት አለባችሁ። እኔን ዘወትር በጸሎት አስቡኝ።◆

**ወንድማችሁ ታደሰ አባተ, ከእስራኤል**




*የሱስ በቅርብ... (ከገጽ3 የዞረ)*

ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ነው ካልን፣ከሱ ጋር ጊዜ ለመውሰድ ፍላጎት ይኖረናል ማለት ነው። ፀሎት ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን ግንኙነት ቁልፍ ነው። ያለ ፀሎት ትክክለኛ ግንኙነት የለም፣ያለግንኙነት ደግሞ እውነተኛ ወዳጅነት የለም። የዘላለም ሕይወት ምንጭ ከሆነው ከየሱስ ጋር እውነተኛ ወዳጅነት ከሌለን ደግሞ መዳናችን ያጠራጥራል ማለት ነው።

4) እግዚአብሔርን እለት በእለት እየተከተልን እናገለግለዋለን።

ጌታ የሱስ እንዲህ አለ፥- «ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም እለት እለት ተሸክሞ ይከተለኝ» (ሉቃ9፥23)። ይህ የማያቋርጥ ግንኙነትን ያሳያል። ይህ ጥቅስ እኛ ከዚህ በፊት ከጌታ ጋር ስለነበረን ልምምድ ብቻ ሳይሆን በየቀኑ ከእርሱ ጋር ለመኖር እንደ አዲስ እንድንወስን ያደፋፍረናል። ይህ የእምነት ልምምድ ከዚህ በፊት ኃጢያታችን ይቅር እንደተባለልን ብቻ ሳይሆን የሚያስታውሰን፣በየቀኑም ስለምናገኘው ድል እና መንፈሳዊ እድገት ያሳየናል። ይህም እራስን መካድና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ኃጢያትን ለመተው ያለንን ውጊያ ያጠቃልላል።

ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ የያዘው ሌላ ሃሳብ ደግሞ፥- ጌታ የሱስ የሚጠይቀንን ሁሉ ለማድረግ እና ወደሚልከን ቦታ ሁሉ ለመሄድ ዝግጁ መሆናችንን ነው። በሌላ አባባል፥- የራሳችንን ፈቃድ ለወደደንና እራሱን ለእኛ አሳልፎ ለሰጠን ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ማስረከብ ማለት ነው። «ሁሉንም ለእግዚአብሔር ስጥ፣ በመሰዊያው ላይ ሁሉንም አስቀምጥ፣ እኔነትን፣ሃብትህን፣ሁሉንም። ወደ ክብር ለመሄድ የሚፈልግ ሁሉ ሁሉንም ማስረከብ አለበት» (ኤርሊ ራይቲንግስ, 66-67)

5) ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እና ስለ እግዚአብሔር ሃይል እንዲሁም ተመልሶ ስለሚመጣው አዳኛችን መመስከር ፍላጎት ይኖረናል

ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ካለን፣ስለመዳናችንም እርግጠኞች ከሆንን ለሌሎች ለምናውቃቸው ሰዎች ስለዚህ መልካም ወዳጃችን የመናገር ፍላጎታችን ይቀሰቀሳል። «በአዳኛችን በየሱስ ሕይወት ውስጥ በሙላት የነበረው ኃጢያተኞችን የማዳን ፍላጎት ከልብ በሚከተሉትም ተከታዮቹ ሕይወት ውስጥ እንዲሁ ይሆናል። ክርስቲያን ለራሱ መኖር አይፈልግም፣ሰዎችን ወደየሱስ ለማምጣት እንጂ። ይህ የእርሱ ሙሉ ፍላጎት ይሆናል (ቴስቲሞኒስ 7 ገጽ 10)።



የሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት እንዲህ ብሎአል፥- «ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፣በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል» (ማቴ24፥14)። እነዚህ ጥቅሶች የየሱስን መመለስ የሚጠብቁትንና ለዚህ ትልቅ ትእይንት መዘጋጀት የሚፈልጉትን ሰዎች ሁሉ ልባቸውን ሊነኳቸው ይገባል። የጸጋ ጊዜ እስከሆነ ድረስ ልንወጣው የሚገባን ትልቅ ኃላፊነት አለብን። የሱስም ተመልሶ የሚመጣው ይህ ሥራ ከተፈጸመ በኋላ ነው። ስለዚህም ነው ወንጌልን የማሰራጨትን ኃላፊነት መወጣት ለዳግም ምጽአቱ ከሚያስፈልጉት ዝግጅቶች ውስጥ ዋናው የሆነው።

**ማጠቃለያ**

አንተ አሁን የት ነው የቆምከው? ኃጥያትህን ተናዝዘሃል? በየሱስም በማመንህና እሱን የሕወትህ መሪ እንዲሆን ካደረግህ ጀምሮ በሕይወትህ ለውጥ አይተሃል? የሱስ ክርስቶስ የየእለት መሪህ እና ወዳጅህ ሆኖአል? እሱን በሙሉ ልብህ ለመከተልና ለማገልገል ፍላጎትህ ነው? ለነዚህ ጥያቄዎች በሙሉ «አዎ» የሚል መልስ ከሰጠህ የሱስ እንደዚህ ይልሃል፥- «ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፣ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም» ለነዚህ ጥያቄዎች ተቃራኒ መልስ ከሰጠህ ግን የዛሬው ቀን ሳያልፍብህ ግንኙነትህን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክል። ተጸጸት፣ንስሃ ግባ፣በየሱስ እመን፣ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት አሻሽል። «ዛሬ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት ካስተካከልክ ክርስቶስ ዛሬ እንኳን ቢመጣ ዝግጁ ነህ» (ኢን ሄቨንሊ ፕሌስስ, 227)። ለደህንነትህ የሚያስፈልገውን ሁሉ ስለሠራልህ እግዚአብሔርን አመስግን። እርሱ ከኃጢያተኞች ሁሉ የሚበልጠውን ኃጥያተኛ ሁልጊዜ ለመቀበል ዝግጁ ነው። ፍቅሩ፣አሳቢነቱ፣ጸጋው እና ኃይሉ ጌታ የሱስ ተመልሶ ሲመጣ ለመቀበል የሚያስችሉንን ነገሮች ሁሉ እንድናገኝ ያደርጉናል።

እግዚአብሔርን በእርግጥ የምታውቅ ከሆነ የዘላለም ሕይወት አለህ። የምንድነውም በእርሱ ጸንተን የምንቆይ ከሆነ ነው፥- ዛሬም፣ነገም፣ከነገወዲያም፣ሁልጊዜ ጌታችን ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ።◆

**ኔይል ዋትስ**

**የዌስት ፓሲፊክ ሚሽን ፕሬዚደንት**
(ከጸሎት ሳምንት ምንባብ የተወሰደ)



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# ራእይ ሲገለጽ

## ተከታታይ ትምህርት



### ራእይ ምእራፍ 4

**በተከፈተው የሰማይ በር ውስጥ አስተውሎ መመልከት**

የእግዚአብሔር መኖሪያ ያለው ከፀሀይና ከጨረቃ ከከዋክብትና ከኦርዮንም አልፎ ምንም አይነት ቴሌስኮፕ የማይደርስበት ቦታ ላይ ነው። ይህ የፈጠረን አምላክ የሚኖረው በጣም ርቆ ሲሆን ለመሆኑ ከእኛስ ሩቅ ነውን?

አዎን! በአንድ በኩል ዙፋኑ ሩቅ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በጣም ቅርብ ነው። ለእኛ ለሰው ልጆች የአለማት ታላቅነትን ለመገመት በጣም ይከብደናል። እግዚአብሔር ራሱ ግን ታላቅ ስለሆነ አለማት ለእርሱ ትልቅ አይደሉም። ስለዚህ ለእግዚአብሔር መላው አለም ልክ እንደ እጁ ጣት ቅርቡ ነው። መለኮታዊ ኃይሉም መላውን የአለማትን እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል።

ሰማይ ለእኛ ሩቅ ስለሆነ ምናልባት እግዚአብሔር ረስቶን ይሆናል ወይንም ስለ እኛ ብዙ ግድ የለውም የሚል ስሜት ሊሰማን ይችል ይሆናል። እንዲያውም እግዚአብሔር ለእኛ በጣም ቅርብ ከመሆኑ የተነሳ በዘካርያስ 2፣8 ላይ እንዲ ተብሎ ተጽፎአል «የሚነካችሁ የዓይኔን ብሌን የሚነካ ነውና» ሉቃስም ላይ በምእራፍ 12፣6,7 ላይ «አምስት ድንቢጦች በአስር ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዷቱ አንኳን በእግዚአብሔር ፊት አትረሳም። ነገር ግን የእናንተ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ አንኳን የተቆጠረ ነው...» ይላል

ይህ ማለት እግዚአብሔር ቀኑን ሙሉ የራሳችንን ጠጉር ቁጥር ሲቀንስና ሲደምር ይውላል ማለት ሳይሆን፣ ጌታ የሱስ ማለት የፈለገው ፈጣሪ ስለየአንዳንዱ ግለሰብ ሁሉን እንደሚያውቅና ስለ ሰዎች ዘወትር እንደሚያስብ ለማሳየት ነው።

እኛ ማሰብ ከምንችለው በላይ እግዚአብሔር ወደ እኛ የቀረበበት ሌላ መንገድም አለ። ይኸውም በየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። በክርስቶስ በኩል አምላክ ከዘላለም መንግሥቱ ወጥቶ ወደ እኛ የሰው ልጆች ክልል ገባ። እስቲ ልብዎትን ከፍተው ከዚህ የሚከተሉትን ጥቅሶች የምሥራች ዜማ ይስሙ፥-

«እግዚአብሔርንም የመምሰል ምስጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው፥ በሥጋ የተገለጠ፣በመንፈስ የጸደቀ፣ለመላእክት የታየ፣ለአሕዛብ የተሰበከ፣በዓለም የታመነ፣በክብር ያረገ» (1ኛ ጢሞ 3፥16) «በመጀመሪያው ቃል ነበር፥ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፣ቃልም እግዚአብሔር ነበር። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር። ... ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፣አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን» (ዮሐ 1፥1,2,14) «በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፤ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፤በምስሉም እንደሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፣ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ» (ፊሊ. 2፥5-8) «ስለዚህ የሕዝብን ኃጢያት ለማስተሰረይ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው። እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላል» (እብ 2፥17-18)

የሱስ የዘለአለማዊው አምላክ ልጅ የእግዚአብሔርን ጸጋና እውነት ለመመስከር፣ የእኛ የአዳም ልጆችን ስቃይና ሲቃ ለመቅመስ ስለኃጢአታችን በመስቀል ላይ ለመሰዋት ብሎ ከዚያም እንደ ታላቅ ወንድማችን ሊቀ ካህናችን በሰማዩ ቤተመቅደስ ሊያማልድልን ብሎ የሰውን አካል ለበሰ።

የሰው ልጅን እድል በቸልተኝነት ለማየት የእግዚአብሔር ልብ አልቻለም። የሱስም አማላጃችን ለመሆን ስለወሰነ በዚህ መንገድ የእግዚአብሔር ዙፋንና መንግሥት ከነሞላው ኃይሉና መለኮቱ ለእኛ ለሰው ልጆች ተጨባጭ ሆነ። (እብ 4፥15-16)

ከሞቱና ከትንሳኤው በኋለም ጌታ ተወካያችን ሁኖ ወደ ሰማይ ተመለሰ በእግዚአብሔርም ዙፋን አጠገብ ቆመ። ለማንኛውም ጥያቄአችን አማላጃችን ሆነ። እንግዲህ ይህንን ሐቅ እንድናውቅና እንድንረዳ አምላክ ስለሚፈልግ የሰማይን በር በጸጋው ከፈተልን። በዚህ መንገድ ስለ እኛ ደህንነትና በየእለቱ ስለሚሰጠን እርዳታ በሰማይ የሚካሄደውን አገልግሎት መረዳት እንችላለን።

**የተከፈተው የሰማይ በር**

የእብራውያን መጽሐፍ ደራሲ የሱስ ከትንሳኤው በኋላ ወዴት እንደሄደ ያሳየናል (እብ 8፥1-2) የራእይ መጽሐፍ ደግሞ በሚያስደንቅ አገላለጽ የሰማዩን ቤተመቅደስ እንድንመለከት ይጋብዘናል።

እስቲ ዮሐንስ ያየውን ራእይ ሲያስረዳን አስተውለን እንመለከት። «ከዚያ በኋላም አየሁ እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምጽ፥- ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን አሳይሃለሁ አለ። ወዲያው በመንፈስ ነበርኩ እነሆም ዙፋን በሰማይ ቆሞአል በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ፣ተቀምጦ የነበረው በመልኩ የኢያስዲድንና የሰርዲኖን እንቁ ይመስል ነበር። በመልኩም መረግድን የመሰለ ቀስተ ደመና በዙፋኑ ዙሪያ ነበር።» (ራእይ 4፥1-3)

በዚህ በተከፈተው በር በኩል ከዮሐንስ ጋር አብረን ስንመለከት እንደ መለከት ድምጽ የሚያስተጋባ ግልጽ የሆነ መልእክት እንሰማለን። ማለትም ወደፊት ስለሚሆነው ገለጻ ሲሰጥ እናያለን። ከመቅጽበትም ከቤተመቅደሱ ውስጥ ማለትም የአለማት ሁሉ መካከለኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን መቀመጫ ዙፋን እናያለን። አገላለጹ በጣም እጹብና ድንቅ ነው። ይህ ዙፋን የመለኮት ኃይል ጥበብና ፍቅር በጠቅላላው የሕይወት ምንጭ የሚፈልቅበት ቦታ ነው።

**በዙፋኑ ዙሪያ ያለው ቀስተ ዳመና**

ዮሐንስ ያየውን እኛም አብረን ስንመለከት በዙፋኑ ዙሪያ ቀስተ ደመና እናያልን። እያንዳንዱ ሐዋርያው በራእዩ ያየው ነገር በሙሉ ትርጉም ያለው ስለሆነ ቀስተ ደመናም የሚያስተላልፈው መልእክት አለው። ቀስተ ደመና የፀሐይ ብርሀንና የዝናብ ውጤት ነው። በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ያለው ቀስተ ደመና የሚየሳየው የምህረትን -የፀሐይ ብርሀን- እና የእውነተኛ ፍርድን ማለትም የእግዚአብሔርን ሁለት ባህሪዎች ነው።

በኖህ ዘመን እግዚአብሔር ምድርን በዝናብ ለማጥፋት በኃጢአተኛ ምድር ላይ እውነተኛ ፍርድን አሳየ። ከዚያም በኋላ ዝናቡ እንዳቆመ ፀሐይዋ ደመና አልፋ ብልጭ አለች። ኖህም የመጀመሪያውን ቀስተ ዳመና ተመለከቶ እግዚአብሔር ምድርን ዳግመኛ በውኀ እንደ ማያጠፋት ተናገረ። (ዘፍ 9፥13-15)

የምህረትና የእውነተኛ ፍርድ ውህደት በማያዛባ መንገድ የተገለጸው ደግሞ በመስቀል ላይ ነበር። በክርስቶስ መስቀል ላይ ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት የእግዚአብሔር ባህሪዎች እናያለን። ማለትም በአንድ በኩል ፍቅሩን በሌላ በኩል ደግሞ ኃጢአትን መጥላቱን።

«ምህረትና እውነት ተገናኙ፤ጽድቅና ሰላም ተስማሙ» (መዝ 85፥10)። እንግዲህ ዮሐንስ ያየው በዙፋኑ ዙሪያ ያለው ቀስተ ደመና ለነዚህ ሁለት የእግዚአብሔር ባህሪዎች ምሳሌ ሆኖ ቆሞአል። «የዙፋንህ መሠረት ጽድቅና ፍርድ ነው፤ምህረትና እውነት በፊትህ ይሄዳሉ» (መዝ 89፥14)

**ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች**

(ቀጥለው ከማንበብዎ በፊት ራእይ 4፥4,10,11 ያንብቡ)

ሌላ በዙፋኑ ዙሪያ የምናየው ደግሞ ሃያ አራት ሽማግሌዎችን ነው። እነዚህ እነማን ናቸው? እነዚህ መላእክት ወይንም የሌላ አለማት ፍጡራን አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትም ቦታ ለመላእክት «ሽማግሌዎች» የሚል ስም አልተሰጣቸውም። ይህ አገላለጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሰው ልጆች የተሰጠና የሰው ልጆችን የሚያመለክት ነው።(1ኛጢሞ 5፥1-2,19፤1ኛ ጴጥ 5, 1-5)። እነዚህ የተጠቀሱት ሽማግሌዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በጣም ከመብሰላቸው የተነሳ የኃላፊነት ቦታ ተሰጥቶአቸዋል።

ዮሐንስ እነዚህ 24 ሽማግሌዎች በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ሲያስቀምጡ ይመለከታል። አክሊል አላቸው ማለትም በምድር ላይ ድል ነሺዎች እንደነበሩ ያሳያል (2ኛ ጢሞ 4፥8 ራእይ 2፥10, 3፥11)

በብሉይ ኪዳንም ማለትም በጥንቱ የቤተመቅደስ ስርአት ውስጥ የ 24 ቱ ሽማግሌዎች አገልግሎትም ይታያል። የብሉይ ኪዳን ቀሳውስት 24ት 24ት በመሆን የቤተመቅደሱን ስርአት ያካሄዱ እንደነበር ይታወቃል። በዚህ አገልግሎታቸው ታላቁን ሊቀ ካህን ይረዱ ነበር (መጽሐፈ ዜና መዋልዕ ቀዳማዊ 24,1-18)

የራእይ መጽሐፍም እንደሚያሳየው እነዚህ 24 ሽማግሌዎች ታላቁን ሊቀ ካህን የሱስን በሰማይ ቤተመቅደስ በሚያደርገው አገልግሎቱ ይረዱታል። በራእይ 5፥8 ላይ «በገናና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ እጣን የሞላበት የወርቅ እቃ» አላቸው ይላል። እነዚህ ሽማግሌዎች በምድር ሕይወታቸው ጊዜ ራሳቸው ደህንነት ያስፈለጋቸው ኃጢአተኞች ሰዎች ስለነበሩ ክርስቶስ እንደ አማላጅ የሚያደርገውን አገልግሎት ትርጉም በጣም ስለሚረዱ ድጋፋቸውን ይሰጡታል።

ይህ ማለት እነዚህ ሽማግሌዎች ቀድሞ በምድር ላይ ሲኖሪ የነበሩ ናቸው። አሁን ግን በሰማይ ከክርስቶስ ጋር ናቸው። ለመሆኑ ወደ ሰማይ የሄዱት መቼ ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ መልስ ሲሰጠን ክርስቶስ ከመቃብር በተነሳበት ጊዜ በመቃብሮቻቸው ተኝተው የነበሩ ጥቂት ሰዎችም አብረው እንደተነሱ ይመሰክራል (ለምሳሌ ማቴዎስ 27፥50-53 ፣ ኤፌሶን 4፥8) ስለዚህ እነዚህ ዮሐንስ በራእይ ያያቸው ሽማግሌዎች ከእነዚህ ከመቃብር ከተነሱት ውስጥ ናቸው።

**ሰባቱ መናፍስትና አራቱ ፍጡራን**

ራእይ 4፥5-11 ያንብቡ።

በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ሳያቋርጥ የሚካሄድ አገልግሎት አለ። 24 ቱ ሽማግሌዎች በእጃቸው የየያዙት እጣን የሚየሳየው በምድር ላይ ያሉትን የእግዚአብሔር ልጆች ፀሎት ሲሆን አሁን ደግሞ ነጸብራቅና ነጎድጎድ ከእግዚአብሔር ዙፋን ሲወጣ እንመለከታልን። በተጨማሪም ሰባት መናፍስትና አራት ፍጡራን እናያለን።

እነዚህ ሰባት የእግዚአብሔር መናፍስት የሚያመለክቱት የጠራውን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሰባት ሳይሆን አንድ ነው። ሰባት ቁጥር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የፍጻሜ፣የሙላት ምልክት ነው።

መንፈስ ቅዱስ በምድር ላይ ለእግዚአብሔር ልጆች የማያቋርጥ አገልግሎትን ይሰጣል። ዮሐንስ የሱስን ልክ -«ሰባትም ቀንዶችና ሰባትም አይኖች ነበሩት» ይላል (ራእይ 5፥6)። የሱስ በምድር የሚኖሩትን ተከታዮቹን ፍላጎት ለማሟላት ብሎ መንፈስ ቅዱስን በሙሉ ኃይል (ሰባት ቀንዶች) እና በሙሉ ጥበብ (ሰባት አይኖች) ልኮታል። መንፈስ ቅዱስም ሰዎች መድህን እንደሚያስፈልጋቸው፣ ልባቸው ወደ ክርስቶስ እንዲሳብ፣ አእምሮአቸውም ኃጢአተኝነታቸውን ተረድቶ ወደ አዳኙ እንዲመጡና ንስሀ እንዲገቡ ከዚያም ስለተቀበሉት ደህንነት ምስክሮች እንዲሆኑ ያሳስባቸዋል።

ዮሐንስ በራእይ ያያቸውን አራቱን ፍጡራን ከረጅም ጊዜ በፊት ኢሳያስና ሕዝቅኤልም በራእይ አይተዋቸው ነበር (ኢሳ6፥1-8 ፣ ሕዝ1፥4-6፣9,10,12-14,16,17,20,21,26-28 ምእ 3፥12)

ኢሳያስና ሕዝቅኤልም ልክ ዮሐንስ እንዳየው የእግዚአብሔርን ዙፋን መቀመጫ የማየት እድል አግኝተው ነበር።

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሶች በሙሉ በአንድነት ባተኩሮ ስንመለከት አራቱ ሕያው ፍጡራን በምድር ላይ በሚካሄደው ነገር ሁሉ ዋና ሚና የሚጫወቱ በኃይል የተሞሉ ፍጡራን እንደሆኑ እናያለን።

- እነዚህ ፍጡራን በእግዚአብሔር ዙፋን አጠገብ ስልጣንና ታላቅ ኃላፊነት

*(በገጽ 8 ይቀጥላል)*


Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com



## የትንቢት መንፈስ

# የተስፋፋው ተቃርኖ (ክፍል 4)

ወድ የትንቢት ቃል አንባቢያን፥ ካለፉት እትሞች ጀምሮ «The Great Controversy» ወይም «ታላቁ ተጋድሎ» ከሚለው መጽሐፍ ውስጥ የመጨረሻዎቹን ሰባት ምእራፎች በተከታታይ በማቅረብ ላይ ነን። ይህ መጽሐፍ በ19 መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ20 መቶ ክ.ዘ. መጀመሪያ ላይ በ ኤለን ጂ ኋይት የተጻፈ ሲሆን ወቅታዊ እውነትን የያዘ በመሆኑ ለአንባቢያን በረከት ይሆናል ብለን እናስባለን።•

እውነትና የእግዚአብሔር ክብር የማይነጣጠሉ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ በእጃችን እያለ በተሳሳቱ አስተያየቶች እግዚአብሔርን ማክበር የማይቻል ነው። ብዙ ሰዎች «የአንድ ሰው ሕይወት ቅንነት ካለው የፈለገውን ቢያምን ምንም የለበትም» ይላሉ። ነገር ግን ሕይወት መልክ የሚያገኘው በእምነት ነው። መንፈሳዊ ብርሃንና እውነትን ለማግኘት እየቻልን እነርሱን የማዳመጥና የማስተዋል ፍላጎታችንን ለማሻሻል ካልፈለግን፤ፈቅደን አንቀበልም በማለታችን ከብርሃን ይልቅ ጨለማን እየመረጥን ነን ማለት ነው። «ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች፣መጨረሻዋ ግን ሞት ነው» (ምሳሌ 16፥25)። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ እየቻልን አለማወቅ ለምንሠራቸው ኃጢያቶችና ስህተቶች ምክኒያት ሊሆን አይችልም። አንድ ሰው ጉዞ በሚጓዝበት ጊዜ መንታ መንገድ አጋጠመው እንበል፤በዚያም ቦታ መንገዶቹ ወደየት እንደሚያመሩ የሚያሳዩ በሁለቱም መንገዶች ላይ የተተከሉ ምልክቶች አሉ። ይህ ሰው ገሸሽ ብሎ በራሱ ግምት ልክ መስሎ የሚታየውን መንገድ ቢወስድ ራሱን በተሳሳተ መንገድ ላይ ያገኛል።

ከእርሱ ትምህርት ጋር እንድንተዋወቅና እርሱ ከእኛ ምን እንደሚጠይቅ እንድናውቅ ሲል እግዚአብሔር ቃሉን ሰጥቶናል። ከሙሴ ሕግ መምህሮች አንዱ ወደ የሱስ መጥቶ «ዘላለማዊ ሕይወትን ለመውረስ ምን ማድረግ ይኖርብኛል?» ብሎ በጠየቀበት ጊዜ መድኃኒታችን «በሕግ የተጻፈው ምንድን ነው? እንዴትስ ታነበዋለህ?» በማለት ወደ መጽሕፍ ቅዱስ አመላከተው። አለማወቅ ታናናሾችንም ሆነ ታላላቆችን ይቅር አያሰኝም፤ወይም ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፍ ሳቢያ ከሚመጣው ቅጣት አያድናቸውም። ምክኒያቱም ሕጉ፣የሕጉ መርህና ሕጉ የሚጠይቀው ነገር ሁሉ በግልጽ ቀርቦላቸው በእጃቸው አለና። መልካም ሃሳብ ብቻ መያዝ በቂ አይደለም። ሰው ራሱ መልካም ነው ብሎ የሚያስበውን ወይም ቄሱ መልካም ነው ብሎ የሚያስተምረውን ማድረግ በቂ አይደለም። እያንዳንዱ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ለራሱ መመርመር አለበት አለበለዚያ የዚህ ሰው መዳን በአደጋ ላይ ይገኛል ማለት ነው። እምነቱ የቱንም ያህል ጠንካራ ቢሆን፣በቄሱ እውነትን የማወቅ ችሎታ የፈለገውን ያህል ቢተማመንም የአንድ ሰው መሠረት ይህ ሊሆን አይገባም። ወደ ሰማይ ቤት ለመጓዝ የሚረዳው ካርታ ስላለው ምንም ነገር በግምት ማድረግ የለበትም።

የማመዛዘን ችሎታ ያለው ፍጡር ሁሉ እውነት ምን እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ መማር፣በተገለጠለት ብርሃን መመላለስና ሌሎችም የእርሱን ምሳሌ እንዲከተሉ ማበረታታት የመጀመሪያውና እጅግ ከፍተኛ ተግባሩ መሆን አለበት። በየቀኑ እያንዳንዱን ሃሳብ በማመዛዘንና ጥቅስን ከጥቅስ ጋር እያነጻጸርን መጽሐፍ ቅዱስን በትጋት ማጥናት አለብን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ የተጻፉት እውነቶች «ታላቅ ጥበብ አለን» በሚሉ ምሁራን «መጽሐፍ ቅዱስ አሁን በምንገለገልበት ቋንቋ ግልጽ ያልሆነ፣ድብቅና ምስጢራዊ ትርጉም(ትምህርት) አለው» እያሉ በማስተማር መጽሐፍ ቅዱስ በጥርጣሬና በጨለማ እንዲከበብ አድርገዋል። እነዚህ ሰዎች ሐሳዊያን መምህራን ናቸው። «መጽሐፍትንና የእግዚአብሔርን ሃይል አታውቁምና ስለዚህ የምትስቱ አይደለምን?» (ማር 12፥24) ብሎ የተናገረው እነዚህን ለመሰሉ ሰዎች ነው። በምሳሌ ወይም በስእላዊ አነጋገር ካልተጻፈ በስተቀር መጽሐፍ ቅዱስ መብራራት ያለበት ግልጽ ሆኖ በተጻፈው ትርጉም መሠረት ነው። ክርስቶስ እንዲህ ሲል ተስፋ ሰጥቶናል፥- «ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል። (ዮሐ 7፥17)። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚነበበው ብቻ ቢወስዱ ኖሮ፣የሚያሳስቱና ግራ የሚያጋቡ የሐሰት መምህራን ባይገኙ ኖሮ መላእክትን ደስ የሚያሰኝና በስህተት ተዘፍቀው የሚንከራተቱትን እልፍ አእላፍ ሰዎች ወደ ክርስቶስ በረት እንዲገቡ የሚያደርግ ተግባር በተከናወነ ነበር።



የተቻለንን ያህል ማስተዋል እንችል ዘንድ በአእምሮ የማሰብ ሃይላችንን ከፍ በማድረግ የእግዚአብሔርን ቃል እናጥና። ሆኖም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮች ለማስተዋል እንድንችል በቀላሉ ሊያስተምሩትና ታዛዥ ባህርይ እንዳለው ሕጻን ሆነን መቅረብ እንዳለብን እንወቅ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ አስቸጋሪ ጥቅሶችን ለመረዳት ልክ የፍልስፍና ምስጢሮችን ለመግለጽ በምንጠቀምባቸው መንገዶች አንጠቀም። መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና አስቀድመን ፀሎት በማድረግ፣በእግዚአብሔር በመመካትና የእርሱንም ፈቃድ ለማወቅ በቅንነት በመሻት እንጂ ብዙ ሰዎች ሳይንስን ለማስተዋል ሲሉ እንደሚያደርጉት በራሳችን መተማመን የለብንም። በትህትናና ለመማር ፈቃደኛ በሆነ መንፈስ «እኔ ነኝ» ወዳለውና ታላቅ ወደሆነው ጌታ እንቅረብ። አለበለዚያ ክፉ መላእክት የእውነት ብርሃን በልባችን እንዳይቀረጽ አእምሮአችንን ይደፍናሉ፣ልባችንንም ያደነድናሉ።

ብዙ ምሁራን «ሚስጥር ናቸው» ወይም «አይጠቅሙም» ብለው ያለፏቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በክርስቶስ ት/ቤት ለተማረው ሰው ሙሉ መጽናኛና ጠቃሚ መመሪያዎች ናቸው። አያሌ የስነ መለኮት ሊቃውንት የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽ የማይረዱበት አንዱ ምክንያት ተግባራዊ ለማድረግ ለማይፈልጉት እውነት አይናቸውን ስለሚጨፍኑ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ማስተዋል የሚቻለው ጽድቅን ከልብ በመሻትና በመናፈቅ ላይ የተመረኮዘ አላማን ይዞ በመምጣት እንጂ በተፈጥሮ ብልህነት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ያለ ፀሎት በጭራሽ መጠናት የለበትም። በቀላሉ ሊስተዋሉ የሚችሉትን ጥቅሶች ጠቃሚነት እንድናስተውል የሚያደርግ ወይም ደግሞ ለመረዳት የሚያስቸግሩትን ጥቅሶች እንዲስተዋሉን የሚያደርግና የተሳሳተ ትርጉም እንዳንሰጥ የሚረዳን መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል እንድናስተውልና በቃሉ ውበት እንድንማረክ፣በማስጠንቀቂያዎቹም እንድንገሰጽ፣ወይም ደግሞ በተስፋ ቃሎቹ ሕይወት እንድናገኝና እንድንጠነክር ልቦቻችንን የሚያዘጋጁት የሰማይ መላእክት ናቸው። የዘማሪውን ተማጽኖ (ፀሎት) የራሳችን ማድረግ አለብን፥- «በሕግህ ውስጥ ያለውን አስደናቂ እውነት ማየት እንድችል አይኖቼን ክፈትልኝ» (መዝ 119፥18)።

ብዙውን ጊዜ ፈተና የማይቋቋሙት የሚሆነው፣ፀሎትንና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ችላ በማለትና፣የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃላት ወዲያውኑ ለማስታወስ ባለመቻልና፤ተፈታኙ መጽሐፍ ቅዱስን መሳሪያው አድርጎ ሰይጣንን ስለማይጋፈጠው ነው። የእግዚአብሔር መላእክት ግን ስነ መለኮትን ለመማር በሚፈቅዱ ሰዎች ዙሪያ ናቸው። እጅግ አስፈላጊ ወቅት በሚያጋጥምበት ጊዜም ለወቅቱ ጠቃሚ የሆነውን እውነት ሰዎች እንዲያስታውሱ ያደርጋሉ። በመሆኑም ጠላት እንደ ጎርፍ ፈሳሽ ቢመጣም የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ አርማውን ያነሳበታል (ኢሳ 59፥19)።

የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ሲል ተስፋ ሰጥቶአል፥- «አብ በስሜ የሚልከው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፣ የነገርኳችሁንም ሁሉ እንድታስታውሱ ያደርጋችኋል» (ዮሐ 14፥26)። ነገር ግን በመከራ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንዲያሳስበን የምንፈልግ ከሆነ የክርስቶስ ትምህርት አስቀድሞ በአእምሮአችን የተቀመጠ መሆን አለበት። ስለዚህም ባለመዝሙሩ ዳዊት እንዲህ አለ፥- «አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» (መዝ 119፥11)።

ለዘላለማዊ ሕይወታቸው ዋጋ የሚሰጡ ሁሉ ጥርጥር እንዳያሸንፋቸው ጥንቁቃን መሆን አለባቸው። የእውነት ምሶሶዎች (መሠረቶች) ጥቃት ይደርስባቸዋል።ፌዝ፣ሽንገላ፣ደባና አለማመን ካለበት ከዘመኑ የሐሰት ትምህርት ለመራቅ አይቻልም። ሰይጣን ለሁሉም መደቦች እንዲመች አድርጎ ፈተናውን ያቀርባል። መኀይሙን (ያልተማሩትን) በዋዛ ፈዛዛ በቀላሉ በማታለል ያጠቃዋል፤የተማረውን ወገን ደግሞ ሳይንሳዊ ቅራኔዎች፣የፍልስፍና ምክንያቶችን ይዞ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲጠራጠሩ ወይም ደግሞ ዋጋ እንዳይጡት በማድረግ ያጠቃቸዋል። እምብዛም የሕይወት ልምድ የሌላቸው ወጣቶች እንኳን ሳይቀሩ የክርስትናን መሠረታዊ አቋም በተመለከተ ጥርጣሬያቸውን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግለጽ ይነሳሉ። ይህም የወጣቶች አለማመን ጥራዝ ነጠቅ ቢሆንም ተጽእኖ አለው። በመሆኑም ብዙዎቹ «የጸጋን መንፈስ እየናቁ» በአባቶቻቸው እምነት ላይ ያፌዛሉ (እብ 10፥29)። ስለዚህ

(በገጽ 8 ይቀጥላል)



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# እግዚአብሔር አዋቂ ነው

## ምስክርነት



እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በመጋቢት 23 1969 ዓ.ም. እንደተወለድኩ ቤተሰቦቼ ይናገራሉ። እናቴና አባቴ እግዚአብሔርን አጥብቀው የሚወዱ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው። ወላጆቼ ክርስቲያኖች ስለሆኑ የክርስትና ጣእሙና ጥቅሙ ሳይገባኝ ቤ/ክ በመመላለስ ዘመናትን ቆጥሬአለሁ። ከቤተሰቦቼና ከክርስቲያን ወገኖች በመደበቅ አጭሻለሁ፣ቅሜአለሁ፣አመንዝሬአለሁ፣ጠጥቻለሁ። ከሰው በመደበቅ ይህንን ክፉ ምግባር ብፈጽምም አምላኬ ከሰማይ ሆኖ ይመለከት ነበር። ሥራ ነገሬ በሙሉ ሞቴን የሚያፋጥኑና ወደ ገሃነም የሚያስሮጡኝ ሆኑ። ለእኔ ያለው አላማ ፍቅር የሆነው ጌታ ግን እድጠፋ፣እንድሞት ዝም አላለም። ሃና ካለችው በላይ እግዚአብሔር አዋቂ ነውና ምንም ሕሊናዬ በማያውቀው፣አይኔ ባልተመለከተው፣እጄም ባልፈጸመው «ወንጀል ሰርተሃል» ተብዬ በ1990 ዓ.ም. ታሰርኩኝ። እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከጥፋት ለመመለስ በብዙ አቅጣጫ ይገለጣል። በበሽታ፣በችግር፣በእጦት፣በብቸኝነት፣በእርዛት እና በተለያየ መንገድ ማንነቱን በመግለጥ ከጥፋት ይታደጋል።

እግዚአብሔር ከሌለበት የእስር ቤት ሕይወት እጅግ መራራ ነው። እና ይህንን መራራ ሕይወት በወህኒ ቤት ተያያዝኩኝ። በድብቅ አጨስ የነበረውን ሲጋራ በገሃድ ተያያዝኩት። ይህም ለአባቴ ተነግሮት አባቴ እያለቀሰ ሲጋራውን እንድተው በአባትነት ምክሩ መከረኝ ልቤ ግን እንዲሁ በቀላሉ የሚታዘዝ አልነበረም። ሌሎች ብዙ አገልጋዮች ቢመክሩኝም ለምክራቸው «የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ» በማለት አሻፈረኝ አልኩኝ። በወህኒ ሆኜ የማወጣውና የማወርደው እቅድ እንደምንም ብዬ ከወህኒ ቤት በመውጣት በገንዘብ ተገዝተው የሀሰት ምስክር በመመስከር የበደሉኝን በሙሉ መበቀል፣መግደል፣ማጥፋት ነበር። በህልሜም በውኔም የማስበው ይህንን ነበር።

ምህረቱና ቸርነቱ ብዙ የሆነ ጌታ እግዚአብሔር እጆቹን ዘርግቶ በፍቅር ሲጠራኝ፣ ሲጠባበቀኝ አላዳምጥ አለኩት፣አስቸገርኩት። ከእለታት አንድ ቀን በ1991 ዓ.ም. የካቲት 20 በድንገተኛ ህመም ታመምኩኝ። እጆቼና እግሮቼ ተኮማትረው ነገር ሁሉ በጨለማ ተዋጠ። ከዚያን በኋላ የሆንኩትን አላውቅም። እስረኞች ተስፋ ቆርጠው እያለቀሱ በእስትሬቸር ተሸክመው ወደ ህክምና ማእከል ከወሰዱኝ ከአንድ ሰዓት ገደማ በኋላ ነፍሴ እንደተመለሰች ይናገራሉ። ከዚያን ጊዜ በኋላም ልቤ አልተመለሰም። በውስጤ ተሰርጾ የነበረው ሃሳብ «እንዴት ባልሠራሁት ወንጀል መከራና ችግር ልንገላታ? ለምን? እንዴት?» የሚል ነበር። ጫት በወህኒ ቤት ስለማይፈቀድ ቡና አስቆልቼና አስወቅቼ እንደጫት ቅሜአለሁ።

ሻይ ለማስፈላት ነው በማለት የሻይን ቅጠል በማስመጣት እንደጫት ቅሜአለሁ። ይህ የምቅመው ጥሬ የሻይ ቅጠል እጅግ እጅግ ክፉ ነው። ያንን የቃመ ሰው ቢያንስ ለአንድ ሳምንት ጤንነቱ ይታወካል። በተከታታይ ለሶስትና ለአራት ቀናት ከፍተኛ የራስ ምታት አይለቀውም። ሃይለኛ የሆድ ድርቀት ያስከትላል። የምግብ ስሜት ለተወሰኑ ቀናት ይጠፋል። እንቅልፍ ይርቃል፣ አቤት መከራ! አቤት መንገላታት! ስንቱ ይዘረዘራል? ይህ ሁሉ የሆነው ዱረሜ ወህኒ ቤት በነበርኩኝ ጊዜ የተከሰተው ታሪኬ ነው።

አሁን ከዚያ ተዛውሬ ወደ ሆሳእና ወህኒ ቤት መጥቼ ነው ያለሁት። መጀመሪያ ከነበርኩባት ወህኒ ቤት ለማምለጥ ብዙ ሙከራዎችን አደረግኩኝ። ጠባቂ ወታደሮች እጅግ ተቸገሩ፣አስተዳደሩም ክርስቲያን ስለነበር ብዙ ጊዜ ወደ ቢሮው በመውሰድ ቢመክረኝም አላደመጥኩትም። በእኔ ምክንያት መላው እስረኞች ሰላማቸው ደፈረሰ፣ታወኩ። እኔም በአመጸኝነቴ በመቀጠሌ ውሾች በሚታሰሩበት ሰንሰለት እግሮቼ ለ17 ወራት ተከረቸሙ። ለአምስት ወራትም በጨለማ ክፍል ታሰርኩኝ። ለመግለጽ የማልፈልጋቸው ብዙ ነገሮች ደርሰውብኛል።። በዚህ ሁሉ ግን ልቤ አልተመለሰም።

በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር በሚያዝያ 10 1992 ዓ.ም. ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ በቃላት መግለጽ ከምችለው በላይ በሆነ በአስደናቂ ብርሃን ውስጥ የኢዮብ ወዳጅ ኤልፋዝ ለኢዮብ በተነገረው በኢዮብ 22፥21 ባለው ቃል ተገለጠልኝ («አሁንም ከእርሱ ጋር ተስማማ ሰላምም ይኑርህ፤በዚያም በጎነት ታገኛለህ»)። በጣም ደነገጥኩኝ፣መገጣጠሚያዎቼ በሙሉ የወላለቁ መሰለኝ፣እግሮቼ በሰንሰለት ታስረዋል፣ሰው ሁሉ ተኝቶአል፣ እኔ ግን ተንቀጠቀጥኩኝ፣አለቀስኩኝ። ያንን በታላቅ ብርሃን ውስጥ ያየሁትን ቃል እስከመቼም አልረሳውም። ወዲያው በራስጌዬ የነበረውን ሲጋራ ሰባበርኩኝ። ከዚያን ሰዓት ጀምሮ በውስጤ የሞላው ደስታ፣ሀሴትና ሰላም በቃላት መግለጽ አይቻልም። በማግስቱ የእስረኞች በር ተከፈተ ከዚህ ቀደም ሁለቱ እግሬ በሰንሰለት ታስሮ ስለነበር ለሽንት የሚወስዱኝ ልጆች ለሁለት እየተሸከሙኝ ነው። በዚያን ማለዳ ግን ማንንም አልፈለግኩም። በአፍጢሜ እንዳልደፋ ተጠንቅቄ እየዘለልኩ ማምለኪያ ቤ/ክ ወዳለበት ደረስኩ። ከዚያም ወደ ቤት ገብቼ በሁለቱም አይኖቼ እንባ እንደጅረት እየፈሰሰ በአምላኬ ፊት ተንበርክኬ ንስሀ ገባሁ። ምን ያህል እንዳለቀስኩ እኔና የሱሴ እናውቃለን። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እኔ የየሱስ ነኝ። ሰይጣን ሲጫወትብኝ ዘመናትን አስቆጥሮአል፣ከእንግዲህ ወዲህ ግን አንገናኝም እግዚአብሔር ለዘላለም ይመስገን። ዛሬ ምንም እንኳን በወህኒ ቤት ብሆንም ሰላሜ እንደወንዝ ይፈስሳል። ከእኔ አልፎ ተርፎ ለሌሎችም ይተርፋል። በምድረበዳ በርካታ የዝማሬ ቅኔዎችን ሰጥቶኛል። በመዝሙርና በጸሎት ጌታን አገለግላለሁ። እግዚአብሔር ብዙ ድንቅ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። «ስርአትህን እማር ዘንድ ያስጨነቅኸኝ መልካም ሆነልኝ» (መዝ 119፥71)። ስሙ ከዘላለም እስከዘላለም የተባረከ ይሁን።

የተወደዳችሁ አንባቢያን፥- ከላይ እንደተመለከታችሁት እንደ እኔ በቤተሰብ እምነት፣በስም ክርስትና ያላችሁ እግዚአብሔር በማይከብርበት መንገድ የቆማችሁ የምህረት አባት እግዚአብሔር እጆቹን ዘርግቶ በፍቅር ሲጣራ፣በተለያየ መንገድ ሲገለጥ አንገታችንን አደንድነን ወደ ዘላለም ሞት እንዳንሄድ አደራ በማለት መልእክቴን አስተላልፋለሁ (ምሳ 29፥1)። የበለጠውን ለመረዳት እናም በደብዳቤ መገናኘት የምትፈልጉኝ አድራሻዬ፥ ሄኖክ ዳንኤል, ፖ.ሳ.ቁ. 153, ሆሳእና እስር ቤት፤ኢትዮጵያ በማለት ታገኙኛላችሁ። ◆

**ሄኖክ ዳንኤል, ከሆሳእና (ኢትዮጵያ)**

---

*<u>የሚቤዠኝ ሕያው ... (ከገጽ1 የዞረ)</u>*

አልችልም!» ይላሉ አዛውንቱ።
«ይችላሉ! እኔ እንድወጣ ከረዱኝ የሕክምናውን ገንዘብ ስለምሰጥዎት የርስዎም ዓይን ብርሃን ያገኛል» ትላቸዋለች። አዛውንቱ በጣም ቅር እያላቸው.... በመጨረሻው ይስማማሉ ከዚያም የጋራ እቅድ ያወጣሉ። ይኸውም በሚቀጥለው ምሽት የአንድ እስረኛ መሞት የሚያበስረውን ደወል እንደሰማች ወዲያውኑ ወደ ሬሳው ቤት ትሄድና የሬሳ ሳጥኑን ከፍታ ከሬሳው ጎን ትጋደምና ሳጥኑን ከላይዋ ላይ ትዘጋዋለች፤በማለዳ አዛውንቱ የሬሳ ሳጥኑን እየነዱ ከእስር ቤቱ ያወጡና ወደ ቀብሩ ቦታ ወስደው ይቀብራሉ በዚያኑ ዕለት ድንግዝግዝ ሲል የመቃብሩን አፈር ያነሱና ነጻ ያወጧታል።
...ወደ ነጻነት የሚመራው ፍጹም እቅድ።

በአንድ ምሽት ሴትየዋ የደወል ድምጽ ትሰማለች «አንድ ሰው ሞቶዋል!» ነው የደወሉ ትርጉም። ለርስዋ ግን ይህ ደወል የነጻነቷን መቅረብ የሚያበስር ደወል ስለሆነ እጅግ በጣም ደስ ይላታል። ወዲያውኑ ኮትዋን ትደርብና ወደ ሬሳ ሳጥኑ ቤት ስታመራ ደብዘዝ ባለ ብርሃን ከክፍሉ ውስጥ አንድ የሬሳ ሳጥን ታስተውላለች። ወድያውኑ በፍጥነት ሳጥኑን ከፍታ ከሬሳው ጎን እንደምንም ብላ ራስዋን አብቃቅታ ትተኛና ሳጥኑን በደንብ አድርጋ ከላይዋ ላይ ትዘጋለች። ከአንድ ሰዓት በኋላ የሬሳው ሳጥን እየተነዳ ሲወጣ ይሰማታል...የነጻነቷ ጊዜ እየተቃረበ ስለሆነ ልቧ በደስታ ይዝላል። ከዚያም የሬሳው ሳጥን ወደ ጉድጓድ ሲገባና በአፈር ሲሞላ ይሰማታል፤ ....በጣም ትደሰታለች።
ቀኑ ወደ ምሽት ተለወጠ ነገር ግን አፈሩ እንደገና ሲነሳ የሚሰማውን ድምጽ ግን አልሰማችም ጊዜው ይሄዳል ምሽቱ ወደ ንጋትነት እንደተለወጠ ትገነዘባለች በዚህን ጊዜ ነገሩ ግራ ይገባታል ያደረገችው ሁሉ በእቅዱ መሠረት ነው ታዲያ ስህተቱ እምኑ ላይ ነው? አዛውንቱስ መች ነው ብቅ የሚሉትና ነጻ የሚያወጧት? ይህች እስረኛ ነገሩ ግራ ገባትና ፈራ ተባ እያለች ክብሪት ትጭርና ከጎኗ ያለውን ሬሳ ታያለች ..... ያ ሬሳ እርሷን ነጻ የሚያወጣት የኒያ የአዛውንቱ ሰውዬ ሬሳ ነበር ... ።

«እኔን ግን የሚቤዠኝ ሕያው እንደ ሆነ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም፣ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ። እኔ ራሴ አየዋለሁ፣አይኖቼም ይመለከቱታል፣ከእኔም ሌላ አይደለም። ልቤ በመናፈቅ ዝሎአል» (ኢዮብ 19፥25-27)። ◆

**ትርጉም፥- ሰለሞን ቁሜ, ከጀርመን**



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# የትንቢት ቃል

Yetnbit Kal
P.O.Box 1749
90006 Nuernberg
Germany

Editors:
Dawit Mehari
Dawit Mengistu

Tel & Fax 0049 - 911- 41 57 89
Tel & Fax 0049 - 89 - 22 24 48
E-Mail: dawit.mehari@mail.com
E-Mail: dawitmengistu@web.de

ይህንን የጽሑፍ አገልግሎት በገንዘብ ለመደገፍ የምታስቡ ሁሉ በዚህ የባንክ ቁጥር መጠቀም ትችላላችሁ። ለድጋፋችሁ በቅድሚያ ከልብ እናመሰግናለን እግዚአብሔር ይባርካችሁ!
Sparkasse Nürnberg,
Yetnbit Kal,
Account Nr.: 2 059 932
BLZ: 760 501 01

ይህች «የትንቢት ቃል» የምትለው የአድቬንቲስት መጽሔት በጀርመን አገር ተዘጋጅታ በየሶስት ወር ትወጣለች። አላማዋም በአገራችንና በተለያዩ አህጉራት የሚገኙትን ወገኖቻችንን ለየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለማዘጋጀት ነው። ምንም ዋጋ የማይከፈልባት በነጻ የምትላክ እንደሆነች ልንገልጽልዎ እንወዳለን። ስለዚህ ለእርስዎም ሆነ ለሌሎች ጽሑፉ እንዲደርሳቸው ለሚፈልጉት ሰዎች አድራሻዎችን ቢያሳውቁን መጽሔቱን እንልካለን።

በዚህች መጽሔት መልእክት ተባርከው እንደሆነና አስተያየትም ሆነ ጥያቄ ካለዎ ሃሳብዎን ቢገልጹልን በጣም ደስ ይለናል።

*ራእይ ሲገለጽ (ከገጽ 5 የዞረ)*

አላቸው። አገልግሎታቸው እስከ አራቱ የምድር ማእዘን ድረስ ይደርሳል አገልግሎት የሚሰጡትም ለሰው ልጆች ነው። መንፈስ ቅዱስ እንደሚፈልገው ለመሥራትና ለመታዘዝ ዘወትር በዝግጅት ቆመዋል። ሥራቸው በጣም የረቀቀና በደንብ የተደራጀ ነው። በአገልግሎታቸው የሚተባበሩአቸውን ሰዎች ይፈልጋሉ። ሰዎችን ለመለኮታዊ ሥራ ለመጋበዝ ስልጣን አላቸው። የአምላክን ቃልም እንዲያስተላልፉ ኃላፊነት ይሰጣሉ። አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙት በታላቅ ፍጥነት ነው። ማለትም ልክ እንደ ነጸብራቅ አራቱ ገጽታቸው ሊያሳየው የሚችለው ፀባያቸውንና አገልግሎታቸውን ነው። የሰው ልጅን ገጽታ መያዛቸው የሚያመለክተው ሰብአዊ የማስተዋል ችሎታና ርህራሄን ሲሆን የአንበሳ ገጽታ ደግሞ የሚያመለክተው ድፍረትን ነው። የበሬ ገጽታ ደግሞ የቆመው ትእግስታቸውን ለማሳየት ሲሆን የንስር ገጽታ ደግሞ ተግባራቸውን ለማከናወን ዝግጁ መሆናቸውን ነው።

ይህ ማለት እነዚህ አራት ፍጡራን የተከበሩ የሰማይ ፍጡራን ሲሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር በመሥራት የደህንነትን ተግባር ይፈጽማሉ። ዮሐንስ ያየው ነጸብራቅና የሰማው ነጎድጓድ ደግሞ የሚያመለከትው የእነዚህ አራት ፍጡራን የማያቋርጥ መሄድና መምጣት ማለትም እንቅስቃሴ፣ የመንፈስ ቅዱስን ሥራና በተጨማሪም መላእክት ለሰው ልጆች የሚያደርጉትን አገልግሎት ነው።

ማንም ሰው ወንድም ሆነ ሴት ሕጻን ሆነ ሽማግሌ በዚህ አገልግሎት ውስጥ አይረሳም። በየአንዳንዱ ሰከንድ በየአንዳንዱ ቀን የሰማይ በረከት በዚህች በአመጽ ላይ ባለች ምድር ላይ ይፈሳል። እያንዳንዱ ፀሎትም ወደ ፈጣሪ ጆሮ ይገባል። መልስም ይሰጠዋል። መንፈስ ቅዱስ በረቀቀው ጥበቡ ለእያንዳንዱ ፀሎት መልስ ለመስጠት ከላይ የተጠቀሱትን ፍጡራን ወደ አስፈላጊው ቦታ ከመቅጽበት ይልካል። የሰማይ ፍጡራን ያለምንም ቸልተኝነት ያለምንም ራስን የመውደድ ስሜት ራሳቸውን ለአገልግሎት አሳልፈው ሰጥተዋል። በዚህ ተግባራቸው እያንዳንዷ ነፍስ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን አጠገብ እንድትመጣ እውነተኛ አገልግሎት ያበረክታሉ። ◆

*የተስፋፋው ... (ከገጽ 6 የዞረ)*

ለእግዚአብሔር ክብር ለአለምም በረከት ይኖሩ ዘንድ ተስፋ የነበራቸው ብዙ ሕይወቶች በአለማመን መርዝ ተመርዘው ጠውልገው ይገኛሉ። ትምክህት በተሞላበት ሰብአዊ ሚዛን ውሳኔ የሚታመኑና መለኮታዊ ምስጢርን ለመግለጽ እንደሚችሉ በማሰብ የእግዚአብሔር ጥበብ ረድኤት ሳይኖርበት ወደ እውነት እንደርሳለን የሚሉ ሁሉ በሰይጣን ወጥመድ የተያዙ ናቸው።

እኛ አሁን የምንኖረው በዚህ አለም ታሪክ እጅግ አስፈሪ በሆነው ወቅት ነው። በምድር ላይ የሰፈሩት እልፍ አእላፍ ሰዎች መጨረሻ ሊወሰን ተቃርቦአል። እኛ የራሳችን የወደፊት ደህንነት የተመረኮዘው በአሁኑ አካሄዳችን ላይ ነው። በእውነት መንፈስ መመራት ያስፈልገናል። እያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ ከልቡ «ጌታ ሆይ ምን እንዳደርግ ትፈቅዳለህ?» ብሎ መጠየቅ ይገባዋል። በጾምና በፀሎት ራሳችንን በጌታ ፊት ዝቅ ማድረግ፣የእግዚአብሔር ቃልን በተለይ ደግሞ የፍርዱን ትእይንት ከልብ ማሰላሰል ያስፈልገናል። በስነ መለኮት የጠለቀና ሕያው የሆነ ልምምድ ይኖረን ዘንድ መሻት አለብን። አንድ አፍታ እንኳን አንዲሁ መባከን የለበትም። አብይት ሁኔታዎች በዙሪያችን እየተፈጸሙ ነው። እኛ ያለነው ዲያቢሎስ በሚፈነድቅባት መሬት ነው። የእግዚአብሔር ጠባቆች አትተኙ! ባላጋራው አድፍጦ እየተቃረበ ነው። ዳተኞችና ያንቀላፋችሁ ስትሆኑም በእናንተ ላይ በመውደቅ ታድኖ እንደሚበላ እንስሳ ሊያደርጋችሁ በማናቸውም ወቅት ዝግጁ ነው።

ብዙዎች በእግዚአብሔር ፊት ስላላቸው ትክክለኛ ሁኔታ የተሳሳተ አመለካከት አላቸው። መጥፎ ነገሮችን ባለመሥራታቸው ይደሰታሉ ቢሆንም እግዚአብሔር ከእነርሱ የሚፈልገውን እነርሱ ግን ለመፈጸም ችላ ያሉትን መልካምና የተከበረ ተግባር መፈጸምን ይዘነጋሉ። እነርሱ የአፀደ እግዚአብሔር ዛፎች መሆናቸው ብቻ በቂ አይደለም። ፍሬ በማፍራት እርሱ ከእነርሱ ለሚጠብቀው መልስ መስጠት የሚኖርባቸው ናቸው።የእርሱ ጸጋ በበዛላቸው ያህል ሊያከናውኗቸው የሚችሉአቸውን መልካም ነገሮች ሁሉ ባለመፈጸማቸው እሱ ተጠያቂ ያደርጋቸዋል። እንደዚህ አይነት ሰዎች በሰማይ መጽሐፍት የተመዘገቡት እንደምድር ሸክም ነው። ሆኖም የእነዚህ ወገኖች ጉዳይም ቢሆን ፍጹም ተስፋ ቢስ አይደለም። የእግዚአብሔርን ምህረት ላቀለሉትና የእርሱንም ጸጋ ላረከሱት ሰዎች በትእግስትና በፍቅር የተመላው የእግዚአብሔር ልብ ይማጸንላቸዋል። ስለዚህም ይላል፥- «አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሳ ክርስቶስም ያበራልሃል፣ ... እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ» (ኤፌ 5፥14-16)

**«አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሳ ክርስቶስም ያበራልሃል»**

(ኤፌ 5፥14-16)

ያ የፈተና ጊዜ ሲመጣ የእግዚአብሔርን ቃል የሕይወታቸው መመሪያ ያደረጉቱ ይገለጻሉ። በበጋ ወራት ወቅት ሁሌም ለምለም በሆኑትና በሌሎች ዛፎች መካከል ጎልቶ የሚታይ ልዩነት የለም። የክረምት ሃይለኛ ነፋስ ሲመጣ ግን ሁሌም ለምለም አትክልት መልካቸውን ሳይለውጡ ይቀራሉ። ሌሎቹ ደግሞ ቅጠላቸው ይረግፍባቸዋል። ስለዚህ አስመሳይ ክርስቲያን አሁን ከእውነተኛው ክርስቲያን ተለይቶ ላይታወቅ ይችላል። ልዩነቱ የሚታይበት ጊዜ ግን ቀርቦአል። ተቃውሞ ይነሳ፣ስደት መከራ ይምጣ፣ሽብርም ይፋፋም፤ያን ጊዜ ግብዝና ገሚስ ልብ ያላቸው ሁሉ ግን ያወላውላሉ እምነታቸውንም ይተዋሉ። ሐቀኛው ክርስቲያን ግን በደህናው ጊዜ ካደረገው የበለጠ ተስፋው ይበልጥ ብሩህ ሆኖ፣እምነቱ ጠንክሮ እንደአለት ጸንቶ ይቆማል።

ባለመዝሙሩ እንዲህ ይላል፥- «ሕግህን ዘወትር አሰላስላለሁ» «ከትእዛዛትህ የተነሳ አስተዋልኩ» (መዝ 119፥99እና104)
«ጥበብን የሚያገኝ ሰው ምስጉን ነው» «በውሃ አጠገብ እንደ ተተከለ፣በወንዝም ዳር ስሩን እንደሚዘረጋ ሙቀትም ሲመጣ እንደማይፈራ ቅጠሉም እንደሚለመልም፣በድርቅ አመትም እንደማይጠጋ፣ፍሬውም እንደማያቋርጥ ዛፍ ይሆናል» (ምሳሌ 3፥13 እና ኤር 17፥8)። ◆

**ኤለን ጂ. ዋይት**

ዲታው
የዋሻ ሰው

ትርጉም በፓ/ር
ጥሩነህ ወ/ሥላሴ

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com